# ስለ ልጅ አስተዳደግ የወላጆች መመሪያ




የመጀመሪያ ህጻንነት መምሪያ
የማህበረሰብና የሰው አገልግሎቶች ክፍል

# የህጻንነት የመጀመሪያ ክፍል



## ተልዕኮ

***ቤተሰቦች በህጻናት ዕድገት ላይ እጅግ የላቀ አስተዋጽኦ አይሪጊ ናቸው፣ ለያንዳንዱ ህጻን ምቹ ሁኔታ ሚፈጡን ለሚጋገጥ ከእያንዳንዱ ህጻን ቤተሰብ ጋር እንሰራለን፡፡.***

## ግቦች

*ተገ ልጋይ ቤተሰቦች ጋር በጋራ መተማመ ግንኙነ ት እናዳብራለን*

*ህጻናትን በማሳደግ ስለምንደግፋቸው ቤተሰቦች ጥንካሬንና ብቃትን ያጎለብታሉ*

*የ ያንዳንዱን ቤተሰብ ማንነ ት፣ ባህላቸዉ፣ ቋንቋቸዉ፣ ልማዳቸዉና ወጋቸዉ ክብር እናበረታታለን፣*

*የቤተሰቦችን የህጻናት እንክብካቤ ዋጋና ልጆቻቸውን በመወከል ያላቸውን የውሳኔ መስጠት መብት እናከብራለን፣ እናበረታታለን፡፡*

*የመጀመሪያ ህጻንነት ዕድገት ተገቢ የሆኑ የህጻናት እንክብካቤዎችን ቤተሰቦችን እንዲገነዘቡዋቸውና ዋጋ እንዲሰጡዋቸው እናበረታታለን፡፡*

*ቤተሰቦች ልጆቻቸውን የመረዳት ሁኔታቸው እንዲያሻሻሉና የልጅ አስተዳደግ ክህሎትና ተግባቦት ወይም መግባባትን በተመለከተ እንዲያጠናክሩ ማድረግ፡፡*

*በማህበረሰብ ሀብትና አገልግሎቶች ድርሻ አማካኝነት በቤተሰቦች ውስጥ የድጋፍ ትስስር መፍጠርና በቀጣይነቱ ላይ መሳተፍ፡፡*

**የይዘት ማውጫ**


መግቢያ........................................................................................ 2

ለቤተሰብዎ ትክክለኛውን አይነት የልጅ አስተዳደግ መምረጥ .............................. 3

ለልጅዎ እንክብካቤ ምርጥ የሆነውን አገልግሎት ሰጪ መምረጥ .................. 5

የህጻናት እንክብካቤ ዝርዝር........................................................... 6

ህጻናት ወይም ድክ ድክ የሚል ህጻን............................................ 8

ቅድመ ትምህርት ቤት ህጻናት ....................................................... 9

ትምህርት ቤት ለመግባት ዕድሜያቸው የደረሱ ህጻናት........................... 10

የልጅ አስተዳደግ ችግሮችን መለየትና መፍታት........................................... 12

ለልጅ እንክብካቤ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ.................................................... 14


## በአሌክሳንደሪያ ከተማ ውስጥ ስለ ልጅ አስተዳደግ መግቢያ

*የአሌክሳንደሪያ ከተማ በከተማው ውስጥ ለሚሰሩትም ሆነ ለሚኖሩት ጥራቱን የጠበቀ የልጅ አስተዳደግ እንዲደርስ ለማድረግ በጽናት ይሰራል፡፡ የማህበረሰብና የሰው አገልግሎት የመጀመሪያ ህጻንነት ክፍል (ኢሲዲ) ቤተሰቦች የልጅ አስተዳደግ አገልግሎትን እንዲያገኙና እንዲጠቀሙ ያግዛል፡፡*

## የመጀመሪያ ህጻንነት ክፍል አገልግሎት

& ስለ ልጅ አስተዳደግ ነጻ መረጃ፣ ማለትም ጥራት ባለው መርሀ ግብር ውስጥ ምን መፈለግ እንዳለባችሁና የአገልግሎት ሰጪዎች ዝርዝር

& ገቢያቸው አነስተኛ ለሆኑ ቤተሰቦች የልጅ ማሳደጊያ ወጪ ለመሸፈን እንዲያግዛቸው የፋይናንስ ድጋፍ

& ህጻናት አሳዳጊዎች ላይ ቤተሰቦች ያላቸውን ቅሬታ መመርመር

&የህጻናት ተንከባካቢ ድርጅቶችና ልጆች ላሉዋቸው ቤተሰቦች ስልጠና፣ ሙያን ማጎልበትና ሌሎች በርካታ ድጋፎች

ስለ ልጅ አስተዳደግ መረጃ እንዴት እናገኛለን፤

- ወደ ኢሲዲ በ ስልክ ቁጥር **703.746.5437** ይደውሉ
- በአካባቢው ህጋዊ የሆኑ የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች በተመለከተ መረጃ ከ **alexandriava.gov/childcare** ይፈልጉ
- በቨርጂኒያ ውስጥ በመንግስት የተፈቀዱ መርሀ ግብሮችን የልጅ ማሳደጊያ ማዕከላትንና የቤተሰብ ልጆች እንክብካቤ መስጫዎችን ጨምሮ በ፣ **www.dss.virginia.gov/facility/search/cc.cgi ይፈልጉ**

## የልጅ ተንከባከቢን መምረጥ የቤተሰብ ዋናው ውሳኔ ነው

ቤተሰቦች ለልጆቻቸው ካሉት ውስጥ ማለትም የህጻናት እንክብካቤ ማዕከላት፣ የህጻናት ትምህርት ቤቶች፣ የቤተሰብ ልጅ እንክብካቤ መስጫ ቦታዎች፣ የቤት ውስጥ አገልግሎት ሰጪዎችና ከትምህርት በፊትም ሆነ በኋላ የህጻናተ እንክብካቤ ከሚሰጡት ውስጥ መምረጥ ይችላሉ፡፡

### የህጻናት እንክብካቤ ማዕከላት

c እድሜያቸው ከስድስት ሳምንታት እስከ አምስት አመታት ለሚሆኑ በቡድን የልጅ እንክብካቤና የምጀመሪያ ህጻንነት ትምህርት ይሰጣሉ፡ ፡
c አብዛኛውን ጊዜ ሙሉ ቀንናአመት ሙሉ ይሰራሉ፡ ፡

c የልዩ አገልግሎት ፈቃድ ከከተማው ማግኘት ይኖርባቸዋል፤ ከዚህም ባሻገር ከቨርጂኒያ ማህበራዊ አገልግሎትፈቃድ የተሰጣቸው ናቸው፡፡

c የተወሰነ የጥራት፣ የመርሀ ግብርና የደህንነት መመዘኛዎችን ያሟሉ፡፡

c በግለሰብ ቤትም ወይም በሞሪያ ፎቆች ወስጥ በጎልሞች አማካኝነት ለአነስተኛ ቡድን እንክብካቤና ለህጻናት የሚጀሚያ ትምህርት ማስጠት፡፡

c ለህጻናትና ለጨቅላዎች ቤት ማስል ወይም ቤት አከልና ኢምደበኛ አካባቢን አገልግሎት ማስጠት

c በከተማው የሚጀሚያ ህጻንነት ክፍል መመዝገብ አለባቸው፡ ፡

c ከከተማው የልዩ ፈቃድ ማግኘትና ከአምስት ህጻናት በላይ የሚንከባከቡ ከሆነ ከአስተዳደሩ (ስቴት) ፈቃድ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

c ተለዋዋጭ የስራ ጊዜ ላላቸው የተለያዩ አማራጮች ይሰጧል

### ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

c እድሜያቸው ለትምህርት ያልደረሱ ህጻናትን በቡድን የህጻናት እንክብካቤና የመጀመሪያ ህጻንነት ትምህርት ይሰጣል፡ ፡

c በተመሳሳይ ዕድሜ ለሚገኙ ህጻናት ላይ ማህበራዊነትንና የመጀመሪያ ትምህርት ላይ ያተኩራል፡ ፡

## ቅድመና ደህረ ትምህርት ቤት የህጻናት እንክብካቤ
## ሞርህ ግብሮች

- እድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ልጆች አዝናኝና ትምህርታዊ ተግባራትን በክትትል በታገዘ ሞርህ ግብር ይሰጣል፡፡
- ከቅድመና ደህረ ትምህርት እንክብካቤ አገልግሎት ከማስጠት ባሻገር ትምህርት በሌለበት ጊዜ ሁሉ ይሰራሉ፡፡
- አንዳንድ ጊዜ በበዓልና በበረዶ ቀናት ጊዜም የእንክብካቤ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡
- በበጋ ሞርህ ግብር ውስጥ ሙሉ ቀን አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

**የአሌክሳንደሪያ ከተማ መስፈርቶች**
**የቤተሰብ ህጻናት እንክብካቤ ቤቶች**

በከተማ ውስጥ ያሉ የልጅ ተንከበካቢ ቤቶች በተመለከተ የሰው ሀይል ምደባ፣ ሞርህ ግብር፣ አካላዊና ከበባዊ ያካተተ መመዘኛዎች አለ፡፡ አምስትና ከዚያ በታች የሚንከባከቡ ሁሉም ቤተሰብ ህጻናት ተንከባካቢ ቤቶች በከተማው የመጀመሪያ ህጻንነት ክፍል መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ምዝገባ ሂደትም የጤና የደህንነት ምርመራን ማለፍ ይኖርባቸዋል፡፡ በቤት ወስጥ ያሉ ጎልማሶች ወንጀልን ለመከላከል ሲባል ስለ ማንነት የሚቀርቡ የሚረጋገጫ ጥያቄዎችን ማለፍ ይኖርባቸዋል፡፡ሁሉም ዕድሜያቸው 14ና ከዚያ በላይ የሆኑት ግለሰቦች የህጻናት አጠባበቅ አገልግሎቶች ማጣሪያ መያዝና የማረጋገጫ ማጣቀሻዎችን ማለፍ አለባቸው፡፡

ከአምስት በላይ ምንም አይነት ዝምድና ለሌላቸው ህጻናት ወይም ከሁለት አመት በታች ለሆኑ ከአራት በላይ ህጻናት እንክብካቤ የሚሰጡ የህጻናት እንክብካቤ ቤቶች ከቨርጂኒያ መንግስት ፈቃድ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ (ይመልከቱ **www.dss.virginia.gov/facility/search/licensed.cgi**)፡፡ የልዩ ፈቃድ አገልግሎቱን ለማግኘት ለከተማው ፈቃድ የተሰጠበት ቤት ይፈልጋል፡፡ሁሉም ምዝገባዎች፣ፈቃዶችና ፈቃድ ምስክር ወረቀቶች በቋሚነት የሚታይ ቦታ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡

መመዘኛ መስፈርቶችንና አስፈላጊ ነገሮችን በበለጠ ለመረዳት፣ እባክዎትን በቨርጂኒያ ማህበራዊ አገልግሎት ክፍል የተዘጋጀውን blication, የህጻናት ተንከባካቢዎችን ለመመረጥና ለመከታተል የወላጆች መመሪያ የሚለውን ሕትመት ይመልከቱ ወይም በቀጥታ በሚከተለው ድረ ገጽ ታገኙታላችሁ **www.dss.virginia.gov/family/ cc/publications.cgi**. እንደዚሁም የከተማውን የምዝገባ መስፈርት በቀጥታ በ **alexandriava.gov/childcare** ማግኘት ይችላሉ፡፡

## ልጅዎን የሚንከባከብ ምርጥ የሆነውን አገልግሎት ሰጪ ለመምረጥ ጊዜ ይወስዳል፡፡

ልጅ ተንከባካቢ በሚፈልጉበት ጊዜ በርካታ ማዕከላትን ወይም ቤቶችን ለመጎብኘት እቅድ ይያዙ፡፡ የአገልግሎት ሰጪዎችንና የማዕከላትን ሰራተኞች ማነጋገር ጠቃሚ ነው፡፡ የአገልግሎት ሰጪውን ቤት ወይም የልጅ መንከባከቢያ ማዕከሉን መጎብኘት ልጅዎ በየቀኑ ለረጅም ሰአታት የሚቆይበትን ቦታ እንዲመለከቱት ያስችልዎታል። ልጅዎ ንቁ ተሳታፊ በሚሆንበት ጊዜና ቀን ጉብኘት ቢያደርጉ ይመረጣል፡፡ ልጅዎን ከርስዎ ጋር ይዘውት ይሂዱ፣ እናም የልጅዎን ሁኔታ ለማጤን ይሞክሩ። ለልጅዎ ምርጥ የሆነውን መርሀ ግብር ለመለየት እንዲያስችልዎት የልጅ መንከባከቢያ ዝርዝሩን ይጠቀሙ፡፡

ማዕከሉን ወይም አገልግሎት ሰጪውን አንዴ ከመረጡ በኋላ አሁንም በድጋሚ ማዕከሉን መጎብኘትና መርሀ ግብሩን ማጤንና ልጅዎን ዘወትር መጎብኘት ያስፈልጋል፡፡ ጥያቄዎች ወይም የሚያሳስብዎት ጉዳዮች ካሉ እነዚህን በመጀመሪያ ከአገልግሎት ሰጪው ወይም ከማዕከሉ ሰራተኞች ጋር ይወያዩ፡፡ ወላጆችና አገልግሎት ሰጪዎች ከተወያዩና አብረው ከሰሩ ብዙ ችግሮች በቀላሉ ሊፈቱ ይችላሉ፡፡



**የልጅ መንከባከቢያን መገምገሚያ ዝርዝር**

እነዚህ ዝርዝሮች እንደ አጠቃላይ መሜሪያ ያገለግላሉ፡፡ ማንኛውንም ነገር በሚርሀ ግብሩ ላይ አገኛለሁ ብለው አይጠብቁ፡፡ ትክክል ነው ብለው የሚያስቡትንና ለልጅዎም ሆነ ለቤተሰብዎ ተስማሚ ነው ብለው የሚሉትን ይምረጡ፡ አጠቃላይ ዝርዝሩን በዕድሜ ተለይቶ ከተቀመጠው ዝርዝር ጋር በማዋሀድ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

# የአጠቃላይ ሞዮ ግብር ጥራት ሚጋገጫ ዝርዝር

## አጠቃላይ ፖሊሲዎች

- ክፍያ፣ ክብረ በአላትንና የህመም ሁኔታን በተመለከተ የፅሁፍ ፖሊሲዎችና መረጃዎች አሉን?
- በመንግስት ወይም በከተማ ማህተም ያረፈባቸው ፈቃዶችና ወይም ምዝገባዎች አሉን፣ ካሉስ ሰነዶቹ የቅርብ ጊዜ ናቸውን ?
- ስለ ልጅዎ ቀን በተመለከተ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ በተንከባካቢው ድርጅት ተጋብዘዋልን?
- ወላጆች በስራዎች ውስጥ ተሳታፊ ናቸውን፣ እንዲሳተፉስ ማበረታቻ አለን?
- ወላጆች የሰራተኛ ወይም የቤተሰብ ህጻን ክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች ወይም ሌሎች መርሀግብሩን ለማመሳከሪያነት የሚጠቀሙ ቤተሰቦች ማመሳከሪያ እንዲጠይቁ ተፈቅዶላቸዋል ?
- በእንክብካቤ ላይ ያሉ ልጆችን ያለ በቅድሚያ ሳያሳውቁ ወይም ሳይደውሉ ልጅዎን መጎብኘት ይችላሉ?

## የሞከሉ ሰራተኞችና የህጻናት እንክብካቤ ሰጪዎች

- በእንክብካቤ ውስጥ ከሚገኙ ልጆች ቁጥር አንጻር በቂ ተንከባካቢዎች አሉን?
- ልጆችን በወቅቱ ክትትል ለማድረግ የሚያስችል መጠነኛ ቡድን ነውን?
- ህጻናቱን በክብር፣ በቅንነትና በትዕግስት ይንከባከቡዋቸዋል?
- ከተሰጣቸው ደረጃ አንጻር ከህጻናት ጋር በወለል ላይ የሚያደርጉትእንክብካቤ ጥሩ ነውን ?
- ልጅዎን ከርስዎ ጋር ለማወያየት ጊዜ ይወስዳሉን?
- ስለ መጀመሪያ ህጻናት እድገት በተመለከተ ልዩ ልምድ ወይም ስልጠና ወይም ትምህርት አላቸውን?
- ጥሩ ግላዊ ንጽህና ያደርጋሉን?
- በህጻናት የመጀመሪያ እርዳታ ወይም ሲፒአር ሰልጥነዋልን?
- ልጅዎ በየቀኑ አንድ አይነት ተንከባካቢ ነው ያላቸው?
- የሰራተኛ መቀያየር ደረጃ ዝቅተኛ ነውን?
- ተንከባካቢዎች ከወቅቱ የህጻናት እንክብካቤ አሰጣጥ ጋር ለመሄድ የሚያስችላቸው በየጊዜው ስልጠና ይወስዳሉን?

### የአገልግሎት አቅርቦቶች

- ከግቢው ወስጥም ሆነ ወጪ ንጹህና ምቹ ነ ወን?
- አስደሳች፣ ብርሃናማ ህብራዊ ነ ወን?
- ነፋሻማና የተስተካከለ ሙቀት ማለትም በበጋ ጊዜ በበቂ ሁኔታ የቀዘቀዘ በክረምት ጊዜ ደግሞ በቂ ሙቀት አለውን ?

- መታጠቢያ ቤቶችና ማዕድቤቶች ንጹህ ናቸውን?
- የቤት ዕቃዎችም ሆነ መሳሪያዎች ለህጻናት ምቹና በቀላሉ ተደራሽ ናቸውን?
- ?በተለያዩ ደረጃ ላሉ ስራዎች በቂ ቦታ አላቸውን ማለትም በቂ ጊዜና ጥሩ ጨዋታ?

**የጤና ደህንነት ማረጋገጫ ነገሮች**

- የልጆች ጥንቃቄ ማስያ አመላካች ነገሮችን አይታችኋል? (ምሳሌ፣ የኤሌክትሪክ መውጫዎች ተሸፍነዋል፣ የህጻናት መግቢያ ደረጃዎች፣ ቁም ሳጥኖች ተቆልፈዋል)
- ህንጻው ሰላምና ደህንነት ቅድመ ማስጠንቀቂያ አሉትን (የእሳት ማጥፊያ፣ የጪስ ማለያ ገብቶላቸዋልን)?
- አደገኛ መድሀኒቶች ወይም አቅርቦቶች ህጻናት እንዳያገኙዋቸው ተደርገው ተቆልፎባቸዋልን?
- አሻንጊሊቶችም ሆነ የመጫወቻ ዕቃዎች በጥሩና በንጹህ ሁኔታ ይገኛሉን?
- የእጅ ማታጠብ ሲዘውተር አይተዋልን ( ከሽንት ቤት ሚልስና ከምግብ ወይም ከቁርስ በፊት) ና ንጽህና (የህጻን የንጽህና ጨርቅ) በተማከተስ ሲዘውተር ተሚልክተዋልን?
- ተዘጋጅቶ የተቀማጠ የመጀመሪያ እርዳታ ቁሳቁስ አለን?
- ለህጻናት የህጻን አልጋ ፣ ለአደጉ ልጆች ደግሞ ስጋጃና አልጋ አለን?

## አካባቢና ሚህ ግብር

- ያሉት አሻንጉሊቶችና ስራዎች ለልጅዎ እድሜ የሚሞጉ ናቸዉን? ለሁሉም ልጆች?
- ያሉት ስራዎች ልጅዎ አዲስ ክህሎት እንዲማርና እንዲያዳብር ያበረታታሉን?



በረካታ የፈጠራ ኪነ ጥበብ ቁሳቁሶች ( የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ስዕሎችና የዕደጥበብ ስራዎች አሉን?

- በደንብ የተደራጀ ነገር ግን ተለዋዋጭ የሆነ የተለጠፈ የስራዎች እቅድ ማለትም በስራና በዕረፍት ጊዜ መካከል ያለዉን ልዩነትና ሚዛናዊነት (ለምሳሌ የወጪ ጨዋታዎች ከግለሰብ ነጻ ጨዋታ ጋር በማጻጻር የሚያሳይ አለን ?
- –የወጪ ጨዋታዎችና የዕረፍት ጊዜዎች በቂና ክትትል ይደረግባቸዋልን?

**ዕሴቶቻችና አሰራሮች**

- ለልጅዎ እንክብካቤ መርሀግብሩንና የአገልግሎት ሰጪውን ግቦች ላይ ይስማማሉ?
- መርሀ ግብሩ የሚያንፀባርቃቸው እሴቶች ከቤተሰብዎ እምነት ጋር ይጣጣማል?
- በተንከባካቢዎች በኩል ልጆች ግጭቶቻቸውን እንዴት እንደሚፈቱ የሚያስተምሩ እንዲሁም ልጆች የንዴት ስሜታቸውን በአግባቡ እንዲገልጹና የተናደዱ ልጆች የሚረጋጉበትን መንገድ እንዲያውቁ የሚያግዙ የሚያደርጉና ለዚህም በጥሞና የሚከታተሉ ናቸውን?
- ተንከባካቢዎች በተለያዩ ዕድሜዎች ላሉ ህጻናት በተጨባጭ የሚጠበቁት ባህሪና ፍላጎቶች አሉን?
- እርስዎና ተንከባካቢዎች ለልጅዎ በእድሜው የሚመጥን አመቺ ስነስርአት ላይ ተስማምታችኋልን?
- በተንከባካቢ ሰራተኞች ዘንድ አዎንታዊ ባህሪን የሚያጠናክሩ ማለትም ምስጋና፣ አድናቆትና ለጥሩ ስነ ምግባር ትኩረት መስጠትን በተመለከተ አይታችኋልን?
- ስነስርአቱ በደንብና ወጥ በሆነ መልክ እየተካሄደ ነውን፣ የፀባይ ማስተካከያዎችስ ያለ ምንም የአካል ቅጣት ወይም ግርፋት ፣ ያለ ምንም ጩኸትና ማዋረድ ነውን?

---

**ህጻናትና ድክ ድክ የሚሉ ህጻናት አያያዥ**— እድሜቸው ከተወለዱ እስከ ሁለት አመት ባለ ጊዜ ውስጥ ያሉ ጨቅላ ህጻናትን አያያዝ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች፡፡.

**አካባቢ**

- የህጻናት ጥንቃቄ መጠበቂያ ቦታ ማለትም ለመንቀሳቀስና ለመጫወት (ምንም ሹል ጠርዝ ቦታ የሌለበት ወይም የሚገለበጥ እቃ የሌለበት፣ ምቹና ንጹህ ወለሎች፣ ከደረጃዎች ውጭ ያሉ ምቹ መግቢያዎች፣ ህጻናት በሚደርሱበት ቦታ ምንም ተሰባሪ ነገር የሌለበት ለማለት ነው)?
- ለመመገቢያ ሆነ የሽንት ጨርቅ ለመቀየር የሚያስችልና ከተጠቀሙ በኋላ በቀላሉ የሚፀዳ ትክክለኛ የህጻናት መንከባከቢያ እቃ አለን?
- በማከባከቢያው ውስጥ ለእያንዳንዱ ህጻን የተለያየ አልጋ አለን?
- መኝታው ምቹና ንጹህ ነውን(የፕላስቲክ ሽፋን ያለው ፍራሽ፣ ለእያንዳንዱ ህጻን የተለያየ መኝታ) አለን ?

**ተንከባካቢዎች**

- ተንከባካቢዎች ለህጻናቱ በአካል ማጫወት ትኩረት (ማቀፍ፣ ማዝ፣ ማጫወት) ይሰጣሉን ?
- ተንከባካቢዎች ለህጻናቱ የሚያነቃቃ ነገር ማለትም ማውራት፣ መዘመር፣እንዲመለከቱት ወይም እንዲነኩት አንዳንድ ነገሮችን ማቅረብ ያደርጋሉን?
- ለልጆች የሚደረገው እንክብካቤ ወጥ፣የህጻኑን አካላዊና ስሜታዊ ፍላጎቶች የሚያሟላ ነውን፣ በመሆኑስ ልጅዎ መታመንና ቅርርቦሽን አዳብሮአል ?

- ልጅዎ በአግባቡ ተመግቧል፣ ለውጥስ አምጥቶአል፣ ተንከባከቢውስ የህጻን እጆችን በየጊዜው ያጥቡዋቸዋል?
- ተንከባካቢው ህጻን ልጅዎን በሽንት ቤት አጠቃቀም ላይ ቀና ትብብር ይሰጡዋችዋልን?
- ተንከባካቢዎች ህጻናት በራሳቸው ነገሮችን እንዲሰሩ ( አሻንጉሊቶችን በቦታው ማስቀመጥ፣ቁልፍ መዝጋት፣ እጆችን መታጠብ፣ ምርጫዎችን ማድረግ-ቁርስን ወይም መጽሀፍትን) ያደርጋሉን ?
- ተንከባካቢዎች በልጅዎችዎ የቋንቋ እድገት ላይ ማለትም ጮክ ብሎ በማንበብ፣ በመዘመር፣ ነገሮችን በስማቸው በመጥራት፣ በማጫወት በተለይም ቁጥሮችንና ሆህያትን ያካተተ ያለበት የጨዋታ አይነትና ውይይት ( ለልጅዎ የንግግር ልውውጥ በመመለስ) ያግዛሉን?

**መርሀ ግብርና ስራዎች**

- ህጻናት የስሜት ህዋሳቸውን የሚያዳብሩበት ነገሮች ማለትም ተንቀሳቃሽ ነገሮች፣ለስላሳ አሻንጉሊቶች፣ ድምጽ የሚያወጡ ነገሮች፣የሚንኳኩ ነገሮች፣ ኳሶች፣ መስታውቶች፣ ወዘተ ማግኘት ይችላሉን?
- ህጻናት አዕምሮአቸውን ለማሰራት ማትም መደርደር፣ችግሮችን መፍታት፣ ሸክላ፣ ነገሮችን ማሽከርከር፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች ወዘተ አመቺ የሆኑ በእድሜ ደረጃ የተዘጋጁ አሻንጉሊቶች አሉን?
- ከግቢ ውስጥም ሆነ ከግቢ ውጭ ልጆችን ለመራመድ እንዲለማመዱ ለመንቀሳቀስ እንዲለምዱና እንዲመረምሩ የሚያደርግና የሚያበረታታ ቦታ አለን?

---

**ቅድመ ትምህርት ቤት ዕድሜ ያላቸዉ ህጻናት አያያዝ** —ይህም እድሜያቸው ከሁለት እስከ አምስት አመት ላሉ ህጻናት ጋር ተያያዥ ጥያቄዎች፡ ፡ .

**አካባቢ**

- ህጻናት ወደ መታጠቢያ ክፍል ለመድረስ የሚያግዙዋቸው መቀመጫዎችና ህጻናት ለመጸዳዳት የሚያገለግሉ መቀመጫዎች አሉን?

**ተንከባካቢዎች**

- ተንከባካቢዎች በምናባዊ ጨዋታዎችና በእደ ጥበባት በመታገዝ ፈጠራዊ ጨዋታዎችን ያበረታታሉን?
- ተንከባካቢዎች ለልጅዎ ባህሪ ምቹ ወሰንና ወጥ ገደብ ሰርተዋልን፣ ምናልባትም ልጅዎ ስህተቶች ቢሰሩ የሚገጥማቸውን ችግሮች እንዲያውቁ አድርገዋልን?
- ተንከባካቢዎች ከልጅዎ ጋር አብረው ይጫወታሉን፣ ስራዎች ጨዋታዎች ላይስ አብረዋቸው ናቸዉን ?
- ልጅዎ ከተንከባካቢዎች አወንታዊና ትዕግስት የተሞላበት ትኩረት እያገኙ ነዉን?
- ተንከባካቢዎች ልጅዎ ነገሮችን በራሳቸው እንዲሰሩ በማድረግ በራሳቸው ብቁ እንዲሆኑና ከስህተታቸዉም እንዲማሩ ያግዛሉን?
- ተንከባካቢዎች ልጆችን በአካል ይናፍቃሉን?

**መርሀ ግብርና ስራዎች**

- ፈጠራንና ምናብን ለማጠናከር የሚያስችሉ አሻንጉሊቶች ( ልብሶች የለበሱ፣ ስዕልና ዕደ ጥበብ ቁሳቁሶች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ የህንጻ ድርድሮች ወዘተ) አሉን?
- o መርሀ ግብሩ ጊዜ ለልጆች ያልታቀደ ጊዜ ወይም ነጻ ጊዜ እንዲኖራቸው ይፈቅዳልን ?
- o ተንከባካቢዎች የአካባቢ መናፈሻ ቦታዎች፣ ቤተ መጽሀፍት ወይም ሌሎች በአቅራቢ ያሉ ማራኪ ቦታዎች ጉብኝት ለሜድረግ አቅደዋልን?

---

***ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች አያያዝ—***ዕድሜያቸው ከስድስት እስከ አስራ ሶስት አመት ያላቸው ህጻናት ጋር የተያያዘ ጥያቄዎች፡፡

**አካባቢ**

- o ዕድሜን መሰረት ያደረጉ ዕቃዎችና ስራዎች አሉን?
- o በቤት ስራቸው ላይ ለማተኮርም ሆነ ለማንበብ የሚሆን ፀጥ ያለ ቦታ አለን?

**ተንከባካቢዎች**

- o ተንከባካቢዎች የልጅዎን የብስለት ደረጃ በሚመጥን መልኩ የተዘጋጁ አስተዳደር፣ ፀጥታና ክትትል ያደርጋሉን?
- o ወጥ የሆነ ውሱኖችና ከልጅዎ የሚጠበቁ የታወቁ ባህሪያት አሉን?
- o እነዚህን ውሱኖች ወይም ድክመቶች ለማስተካከል ተንከባካቢዎች ፈቃደኞች ናቸውን?
- o ተንከባካቢዎች ህጻናት በሚያድጉበት ጊዜ የሚያሳዩትን ተጋጭ የሆኑ ስሜቶችንና ውዥንብሮችን በተመለከተ መመሪያ ወይም ግንዛቤ ይሰጣሉን?
- o ተንከባካቢዎች ከህጻናት ለሚወጡ አስተያየቶችና ሀሳቦች ክብር ያሳያሉን?
- o ተንከባካቢዎች ልጆች ለመረጡዋቸው ምርጫዎች ሀላፊነት እንዲወስዱ ይፈቅዳሉን፣ በቤት ስራቸው፣ በፕሮጀክቶቻቸውና በቤት ስራዎቻቸው ላይ ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶች ይሰጡዋቸዋልን?
- o ተንከባካቢዎች የትላልቅ ልጆችን የአቻ ተጽዕኖ ስሜት፣ የጾታና የማንነት ትግል ሁኔታ ይረዱዋችዋልን?
- o ተንከባካበዎች ልጅዎን ያዳምጡ፣ ትኩረት ያደርጋሉን?

***ሞርሀ ግብርና ስራዎች***

- o መርሀ ግብሩ ወይም የእቅዱ ሰሌዳ ለቤት ስራ ጊዜ ይሰጣልን?
- o ሀይል በሚጠይቁ ጨዋታዎች ማለትም የቡድን ስፖርት ወይም ሌላ የአካል እንቅስቃሴ ላይ ለመሳተፍ ዕድሉ አለን?

- መርሀ ግብሩ የልጅዎን ልዩ ፍላጎት ማለትም ሙዚቃ፣ ኮምፒውተር፣ ሞዴሎች፣ የግበ ማስዋብ ስራ፣ የፎቶግራፍ ስራ፣ ማሰባሰብ ፣ ወዘተ ያግዛልን?
- የዕቅዱ ጊዜ ሰሌዳ ወይም መርሀ ግብሩ ከትምህርት በኋላ ልጅዎ ከጓደኞቻቸው ጋር የማህበራዊ ጊዜ እንዲኖራቸው ይፈቅዳልን?
- በፕሮግራሞቻችሁ የምትጠቀሙባቸው ልዩ አገልግሎቶች ማለትም የማህበረሰብ ማዕከል፣ መዝናኛ፣ ጂም አሉን?



**የቤተሰብዎ ጥያቄዎች**

ይህ ቦታ የተተው የልጅችዎን ልዩ ፍላጎት በተማከተ ተጨማሪ ጥያቄዎችን እንዲያሰፍሩበት ነው፡፡ጥያቄዎችዎን መጻፍና መወያየት ለጥያቄ ከሜድዎ በፊት ለማስታወስ ምናልባትም ከዚያም በኋላ ለልጅዎ ተስማሚ ምርጥ የሆነውን ተንከባካቢ ድርጅትን ለማምረጥ ያግዝዎታል፡፡.

## የመጥፎ የልጅ እንክብካቤ ወይም አያያዝ ለመለየት ማስጠንቀቂያ ምልክቶች…

በዚህ አለም ውስጥ፣ እንደሚታወቀው፣ ከለውጥ በስተቀር የማይለወጥ ነገር የለም፡፡ የህጻናት አያያዝ መርሀ ግብርም ከዚህ የተለየ አይደለም፣ በመሆኑም በመጥፎ ወይም በጥሩ ሁኔታ ይለወጣል፡፡ ከዚህ በታች ያሉት በልጆች እንክብካቤ ማዕከል ወይም አገልግሎት ሰጪ ዘነድ የሚከሰቱ ችግሮች ናቸው፡፡

**ያልተነገሩ ጉብኝቶች** ይፈቀዳሉ፣ ወላጆች ጉብኝቱን ለማድረግ መደወል ይኖርባቸዋል ወይም ልጆቻቸውን ከተለመደው ሰአት ቀደም ብለው ለማውጣት ከፈለጉም እንደዚሁ መደወል ግዴታ ነው፡፡

**ወላጆች** በልጅ እንክብካቤ **መስጫ ቦታ አይፈቀድላቸውም፣** ልጅዎን ሜከሉ በሮ ወይም እንግዳ መቀብያ ወይም የቤተሰብ ልጅ ተንከባካቢው ቤት ፊት በር ትተው እንዲሄዱ ነው፡፡

**ልጅዎ አልተስተካከልም፣** ለበርካታ ወራት ቢያልፍም ወደ ሜከሉ በሜዱ አልተደሰቱም ወይም በድንብ ተስተካክሎ የነበረው ሰው ድንገት ደስተኛ ሊሆን አልቻለም፡፡ ይህ አደገኛ ምልክትም ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፣ ልጆች በተለያየ ዕድሜ የመለያየት ዕጣ ፈንታ አጋጥሞአቸው ነበር፣ ነገር ግን ይህን ማጣራት ተገቢ ነው፡፡

**ልጅዎ የፈራ ይመስላል** ወይስ የሆነ ተንከባካቢ ሰው ጠልተዋል ወይስ የፈሩ ይመስላል፣ በጣም ፀጥ ብለዋል፡፡

ልጅቸን የሚከባከቡ **የማያውቋቸው ሰዎች አይተዋል**፣የተለያዩ ሰራተኞች ወይም በየጊዜው የሰራተኞች መቀያየር ይኖራል፡፡

**እንክብካቤው ልዩነት የሌለበት ወይም የላላ ሊሆን ይችላል፣** ልጆች ያለ ማንም ተከታታይ ከውጭ እየተጫወቱ ይተዋሉ ወይም ትኩረት ለማግኘት ረጅም ጊዜ መጠበቅ ሊኖርባቸው ይችላል፡፡

ተንከባካበዎች ያላስተዋሉት በመሆኑም ምክንያቱን መግለጽ የማይችሉበት **በልጅዎ ላይ ቁስለት ወይም ጉዳት ሊኖር ይችላል፡፡**

**የተንከባካቢው ሁኔታ ወይም** ድምጽ አስፈሪ፣ ጨካኝና ሁሉንም ህጻናትን በእኩል አይን የሚያይ ሊሆን ይችላል፡፡

**ጥቂት የሚባሉ ተግባራት** ወይም አሻንጊሊቶች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ሆኖም ግን አሻንጉሊቶች ለማከመቻል ለዕይታ የቀረቡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ተንከባካበዎች ተነጫጪ፣** ግትር ወይም አጋዥ ያልሆኑና ወይም በጉዳዮች ላይ መወያየት የማይፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**በእንክብካቤው ጥሩ ነገር አልተሰማችሁም፣ በተንከባካበዎች ላይ እምነት የላችሁም ወይም ልጅዎችዎ ምን እየሰሩ እንደሆነ አስጨንቅዎታል፡፡** በዚህ ጊዜ ከልጅዎ ጋር ሆነው ጊዜ ወስዶ በመነጋገር ነገሮችን በቀጥታ እንዲገነዘቡ ያስችልዎታል፡፡

# ከልጅዎ ተንከባካቢ ድርጅት ጋር ችግር ቢከሰት ምን ማድረግ አለብዎት፡ ፡

በልጅዎ የእንክብካቤ ማዕከል ግብር ጥሩ አዝማሚያ ከሌለና ችግሮችን ከለተማለከቱ ወዲያወኑ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡ ፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡ ፡

**ችግር ካለ…**
…**ከማእከሉ ወይም ከቤቱ በአሰራር ጋር የተያያዙ ችግሮች** ማለትም የአሰራር ሂደት፣ ክፍያዎች ወይም ፖሊሲዎች ሲኖር ከርዕሰ ማዕከሩ ወይም ከሚማለከቶው ሰው ጋር ቀጥሮ በማያዝ ማነጋገር፡ ፡

**… ከተንከባካቢው ጋር በተያያዘ ደግሞ ማስተሚያ ክፍሉ፣** የማስተሚያው ዘዴ ወይም በርስዎ ልጅና በሌሎች ልጆች ግጭት ሲኖር ችግሩን ለመፍታ ከተንከባካቢው ጋር ቀጥሮ በማያዝ በሰላም መፍታት፡ ፡ ይህን ነገር ልጅዎችን ሲቀበሉ ወይም ሲያደርሱ ለመፍታት አይሞክሩ፡ ፡

**…ከተንከባካቢው ጋር የተወያዩት** የመፍትሄ ደረጃ እርስዎ ያልተስማሙበት ወይም ያልረኩበት ከሆነ ከርዕሰ ማዕከር ጋር መወያየት በዚህን ጊዜ ግን ከተቻለ ብቻዎን ሳይሆኑ ያ መጀመሪያ ወይይት ያደረጋችሁት ተንከባካቢን መጥራት አለብዎት፡ ፡

**…ልጆችን አደጋ ላይ የሚጥል** ይህም ሲባል ህግን በመጣስ የሚደረግ ከሆነ ለምሳሌ በእንክብካቤ ማስጫ ቦታው ላይ በርካታ ልጆች መቀበል ወይም የደህንነትና የጤና ችግሮች ቢኖሩና ድርጅቱ ይህን ችግር ለመፍታት ካልተነሳሳ ለኢሲዲ በዚህ ስልክ ቁጥር 703.746.5437 ይደወሉ፡ ፡ ማዕከ ግብሩ ማእከል ከሆነ ግን የስቴት ፈቃድ ሰጪው በ ስልክ ቁጥር 703.934.1505 ያሳወቁ፡ ፡

**ችግሩን ይፍቱ!**

ችግሮችን ለመፍታት ውጤታማ ስብሰባ ለማድረግ የመፍቻ ሞዴልን ይጠቀሙ፡ .

ማንንም ሳይወነጅሉ ችግሩን **ይዘርዝሩ፣** *"እኔ ያገባኛል ምክንያቱም ድርጊቱ ተከስቷል"* ወይም

*"እኔ አይቻዋለሁ____ እናም ብንወያይበት ደስ ይለናል?" እንደዚህ አይነት ቃላት ለመጀመሮ ጥሩ ናቸው፡*

ችግሮችን ለመፍታት ሀሳብ እንዲያወጡ **ይጋብዙ፡፡** ከዚያም እናንተና አገልግሎት ሰጪው መሞከር ያለባችሁን ነገር ወስኑ፡፡

**ያድምጡና** ፀጥ ብለው ይቆዩ፡ ፡ .

ለአገልግሎት ሰጪው **ዋጋ ይስጡ፡፡**. እንደምታደንቁዋቸው ንገሩዋቸው ከዚያም ከነርሱም በጋራ እንደምትሰሩና መፍትሄም በጋራ ለመፈለግ ፈቃደኛ እንደሆናችሁ ንገሩዋቸው፡፡

ከጥቂት ቀናት ወይም ሳምንታት በኋላ አገልግሎት ሰጪዎችን በማነጋገር፣ ስሜታችሁን በማካፈል እናም የነርሱንም ስሜት ይጠይቁዋቸውና **ይገምግሙ፡**

# ለጥቂት የአሌክሳንድሪያ ቤተሰቦች ለልጆች እንክብካቤ የሚጠየቅን ክፍያ የሚያግዝ በተመለከተ ፡፡

ለልጆች እንክብካቤን በተመለከተ የገንዘብ ድጋፍ ለማመልከት ሁሉም ወላጆች ማሟላት የሚገባቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፤

- ✓ **የቅጥር ሰራተኛ የሆኑ መሆን employed**,
- ✓ ስራ ለማግኘት በትምህርት መርሀ ግብር **የተመዘገቡ** ወይም
- ✓ ስራና ትምህርትን በማጣመር **የሚሳተፉ፡፡**

ለገንዘብ ድጋፉ ተቀባይነት ለማግኘት በርካታ ጉዳዮች ተጽዕኖቸውን ያሳርፋሉ፤ ከነዚህም ውስጥ አጠቃላይ የቤተሰብ ገቢ(ወላጆች በአጠቃላይ የሚያገኙት ገቢ ግብርንና ሌሎች የገቢ ምንጮችን አጠቃሎ በሚያዝ ማለትም የልጅ ድጋፍ )፣ እና በቤት ውስጥ የሚኖሩ የቤተሰብ አባላት ብዛት፡፡

**ቤተሰብዎ ይመለከትዋል ብለው ካሰቡ ወደ አሲዲ በስልክ ቁጥር 703.746.5437 ይደውሉ፣ ማመልከቻ ለማቅረብም በሮ ይምጡ ወይም በቀጥታ በድረ ገጽ አድራሻ commonhelp.virginia.gov. ያመልከቱ፡፡**

አሲዲ ማመልከቻውን ለርስዎ ይልከልዎታል ወይም በወቅቱ ለድጋፍ የሚውል መዋጮ ከሌለ ስምዎትን በተጠባባቂ ዝርዝር ያስቀምጥልዎታል፡፡

**የማመልከቻውን ቅጽ ይሙሉ፣** ምናልባት ድጋፍ ካስፈለግዎት ወይም ጥያቄ ካለዎት ይደውሉ፡፡ቅጹን ሞልተው ሲጨርሱ

ከአስፈላጊ ሚጃዎች ጋር ለአሲዲ ይመልሱት፡፡ ማመልከቻዎ ከታየ በኋላ ፣ **የህጻናት እንክብካቤ ሰራተኛ** ስለ

ልጅ እንክብካቤ ፍላጎትና ስለርስዎ ተቀባይነት ሁኔታ ለመወያየት ቀጠሮ ለማያዝ ያገኝዎታል፡፡

## ለወላጆች ሌሎች ጠቃሚ  ነገሮች

### የህጻናት ወላጅ  ትምህርት መርሀ ግብር (ፒአይ ኢ)

የአሌክሳንደሪያ ከተማ ፒአይ ኢ መርሀ ግብር እድሜያቸው እስከ ሶስት አመት ለሆኑ ህጻናትና አካላዊ ወይም አምሮአዊ እድገታቸው ከተጠበቀው በታች የሆነ ወይም የዘገየ ማለትም በምርመራ ሀያ አምስት በመቶ በአንዱ ወይምበተጨማሪ ሌሎች የዕድገት ሁኔታዎች ዘገምተኛነት ያሳዩ ቤተሰቦች ጋር ይሰራል፡፡ ፒአይኢ የቨርጂኒያ የህጻናት ግንኙነት ክፍል ነው፡፡ የሚይዛቸው አገልግሎቶች፤

- የሚከተሉትን ጉዳዮች ለመገምገም የህጻናት ግምገማ፡
  ግንዛቤ፣ አካለዊ፣ ተግባቦት፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊና የተላመዱ ተግባራት
  የግለሰብና የቤተሰብ ፍላጎት፣ እና እነዚያን ግላጎቶች ለማሳካት   እቅድ ማውጣት
- የእድገት ትምህርት ለወላጆች ይሰጣል በዚህም ቤተሰቦች ልጆቻቸውን እንዲዳብሩና እንዲማሩ ያግዛቸዋል፡፡
- ድጋፎቸንና አገልግሎቶችን ለማለ,መልከትና ለመጠቀም የአገልግሎት ትብብር  ያግዛል
  በልጆች ተፈጥሮአዊ አካባቢ ማለትም ቤት ወይም ቅድመ ትምህርት ቤት
- ለልዩ አገልግሎቶችና እቃዎች የገንዘብ ድጋፍ  ( እንደተገኘ)

**የህጻናት ወላጅ  ትምህርት መርሀ ግብር  ለበለጠ መረጃ  በዚህ ስልክ  ቁጥር  ይደውሉ 703.746.3350.**

### ቅድመ ትምህርት ቤት መከላከል መርሀ ግብር

የቅድመ ትምህርት ቤት መከላከል ቡድን ከአሌክሳንደሪያ ከተማ የመጀመሪያ ልጅነት ማህበረሰብ ጋር በመሆን እድሜያቸው ከዜሮ እስከ አምስት ለሆኑ ህጻናት ጤናቸውን፣ ማህበራዊ ስሜታቸውን ለማሳደግ የተንከባካቢዎችንና የልጆችን ግንኙነት በማጠናከር ይሰራል፡፡የቅድመ ትምህርት ቤት መከላከል ቡድን ያቀፋቸው የአዕምሮ ጤና ባለሙያዎችን ሲሆን እነሱም እገዛ የሚያደርጉት፡:

- ለቅድመ ትምህርት ቤት መምህራንና ቤተሰቦች አሳታፊ የሆነ የፊት ለፊት ስልጠና
- ለህጻናትና ለቤተሰቦች ደጋፊ ምክር
- ወላጅ ማማከር
- የህጻናት ማህበራዊ ክህሎት እድገትና ባህሪ አያያዝ

**በአሌክሳንደሪያ  ህጻናት  ማከል  የቀረበወን  ስለ  ይፋዊ   የጨዋታ  በድን  በተማከተ ለበለጠ  ሚጃ    ይህንን  ይጉብኙ**
**www.centerforalexandriaschildren.org.**

**ስለ  ቅድመ ትምህርት  ቤት  መከላከል  በድን  አገልግሎት  ለበለጠ  ሚጃ  በስልክ ቁጥር   703.746.6009 ይደወሉ፡ ፡**

# ማስታወሻ